# ዝናብ ወደ ላይ መዝነብ ሲጀምር

ብዕር ከተባለ - ቪ.ል፤ ስዊዘርላንድ

መቻቻል 2ኛ ዓመት ቁ.1 (ጥር Jan.2000)

በአሜሪካን መንግሥት መሪነት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በመንግሥታት ርብርቦሽ የተዋቀረውና የተቋቋመው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (UN) ከመመሪያዎቹና ኃላፊነቶቹ ሁሉ የመጀመሪያው የዓለማችንን ሠላም መጠበቅ ነው። በአጭሩ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላለፉት 50 የሚሆኑ ዓመታት የምድራችንን ሠላም በተመለከተ የሠራቸውና ያበረከታቸው አስተዋፅዖች ሲገመገም ኃላፊነቱን በሚገባ እንዳልተወጣ (ያበረከታቸው አስተዋፅዖች-ጠንካራ ጐኖች እንደተጠበቁ ሆነው) ግልፅ ነው። ምናልባትም የዚህ ምክንያት ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው የትዔለሌ የሆነው unwield bureaucracy የተሸከመው ዓላማ የዓለምን ሠላም ለመጠበቅ «Rocking the boat» ሣይሆን አይቀርም። ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኃላፊነቱ ኪሣራ ዋነኛው ምክንያት ሣይወሣ ሊታለፍ የማይገባው እንደ ዩናይትድ ስቴትስ የናጠጡ «የጦር ከበርቴ መሰል» መንግሥታትና ተከታዮቻቸው ዓለምን ለመቆጣጠርና በእጅ አዙር ለመግዛት የሚያደርጉት ጥረት ነው። ለዚህም ይመስላል ሠላምን የሚያናጋ ችግር በተፈጠረ ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት ወደ ኋላ የሚቀረውና እንዲቀርም «የሚገደደው»።

አንድ ቁምነገር እንዳይረሣ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን እንዲመሰገን፤ ስሙን ከሚያስጠሩት ሥራዎች አንዱና ብቸኛው የምድራችንን ገፅ በሞሉት ከ200 በላይ በሚሆኑ ድንበራትና አገሮች ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው የመረጃ ስብሰባ ነው። በምሣሌነት - The Human Development Report ብንወስድ ለ10 ዓመታት መረጃው ያለ ማቋረጥ ምን ያህል የዓለማችን ህፃናት ትምህርት ቤት እንደሚሄዱ፤ ምን እንደሚበሉ (የምግቡን ዓይነትና መጠን)፤ ንፁህ ውሃ የሚገኝባቸው ቦታዎች፤ ሴቶች ምን ያህል የምጣኔ ሃብት ደረጃ እንደሚያበረክቱ (በጉልበት ደረጃ)፤ ምን ያህሎቻችን በቀላሉ ልንከባከባቸው ከምንችለው ነገር ግን እስከ ሞት ሊያደርሱን ከሚችሉት በሽታዎች ክትባት እንደምናገኝ ወዘተ...

እ.ኤ.አ. 1999 የሐምሌ ወር እትም (መረጃ) በዝርዝር የሚመረምረው ምን ያህሉን የዓለማችንን Goods & Services ሃብታምና ደሃው ክፍል እንደሚቀራመቱት ነው። በመረጃው መሠረት US $24 trillion በዓመት የዓለማችን ፍጆታ ÷ World's Consumption bill ሲሆን ከላይ ያሉት አምስቱ ባለጠጋ አገሮች 86% የሚሆነውን ለብቻቸው ሲግጡት ÷ ከታች የሚገኙት አምስት ደሃ አገሮች (ኢትዮጵያን ጨምሮ) 1.3% ብቻ የምትሆነውን ይቋደሟሉ።

እኒያ አሜሪካውያን $8 billion በዓመት ውበትን ማደሻ ለሆኑ (Cosmetics) ሲያፈሱ በአንፃሩ ይህን ያህል ገንዘብ በምድረ ገፅ ለእያንዳንዱ መሠረታዊ ትምህርትን ለማስጨበጥ ከሚገመተው $2 billion መብለጡን ስንሰማ የሚገርም ሆኖ እናገኘዋለን።

አውሮፓውያን ብቻ ወደ $11billion በየዓመቱ ለዚያች ተመጣጭ በረዶ Ice- Cream ያወጣሉ። ይህን ተመጣጣኝ ግምት የሚያህል ገንዘብ ዓለማችንን በንፁህ ውሃና በአንፃራዊነቱ ጥሩ ከሚባለው ፍሣሽ (sewers) ባንበሸበሻት ነበር።

በታዳጊ አገሮች ውስጥ ለሚገኘው 4.4 billion ከሚሆነው ሕዝብ ከምስት ሁለቱ ብቻ የውስጥ ለውስጥ የፍሣሽ (sewers) ተጠቃሚ ሲሆኑ ከሦስት አንዱ ደግሞ በጭራሽ የንፁህ

ውሃ ተጠቃሚ አይደሉም። ረሃቡ አሁንም የዚሁ የታዳጊው የፈረደበት ዓለም ሕዝብ ጥሩ የሚባል የመኖሪያ ቤት የለውም። አንድ አምስተኛ የሚሆነው የዚሁ የግዙፍ ቁጥር አካል ከዘመናዊ የህክምና ዘዴዎች አንዱም አይደርሰውም።

በጣም አሣዛኝ የሆነ ነገር ግን አዲስ ያልሆነው ነገር ቢኖር ሃብታም በሃብቱ እየከበረና እየናጠጠ ሲሄድ ደሃው ደግሞ በተገላቢጦሹ እየመነመነና እየደኸየ መሄዱ ነው።

ይህ ሪፖርት ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት የአምስቱ የበለፀጉ አገሮችና ከደረጃው በታች የሚገኙት የአምስቱ ታዳጊ አገሮች የገቢ ምንጭ ንፅፅር ከ60:1 ወደ 74:1 ማሸቀቡ ብሎም ወደ ሰማኒያ የሚጠጉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል አገሮች ከፊሉ ከጥቅሉ መሆኑም አይደል ዛሬ ጊዜ ቆርቁዘው፣ ደህይተው ከ20 ዓመታት በፊት ከነበሩበት ደረጃ አቆልቁለው መገኘታቸውን ያስረዳናል።

የአንድ አፍሪቃዊ ቤተሰብ ማዕከላዊ ኑሮ ይገፋል ተብሎ የሚታሰበው ከዛሬ 25 ዓመታት በፊት ይጠቀም ከነበረው በ20% ያነሰ ፍጆታ በጀቱን እንዳናጋው ጥናቱ ይጠቁማል።

ድልቡን ሃብት ያጋበሱት 225 የሚሞሉት የምድራችን ባለጠጐች ውስጥ 60ዎቹ አሜሪካውያን (በዜግነት) ሲሆኑ፣ $311 billion የሚመጥን ቋሚ ሀብት (assets) ሲኖራቸው ፀጋቸው (wealth) በድምሩ ወደ $1 trillion ይጠጋል። ይህ ማለት ደግሞ ወደ 47% የሚጠጋውን ደሃውን የዓለማችን ክፍል የዓመት ገቢውን ይስተካከለዋል።

ኧረ ምኑን ጉድ አወረደው እንዳው! ሦስቱ ብቻ የዚሁ የሃብቱ መሠላል የላይኛው ተንጠልጣዮች (ግለሰቦች) 48 ያህሉ ታዳጊ አገሮች ካላቸው የጥምር «Gross Domestic Product/GDP» የበለጠ መሆኑን ጥናቱ አሁንም በአበክሮ ይጠቁማል።

እዚህ ላይ ሊታወስ የሚገባው ነገር ቢኖር፣ የምጣኔ ሃብት ዕድገት ወደታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል የሚዘንብ ሣይሆን ወደላይኛው (ወደላይ መዝነብ እሚባል ነገር ካለ! ) ነው። ለዚህ የተዛባ የሃብትና ብልፅግና፣ የክምችትና የአጠቃቀም ልዩነት ዋነኛ ምክንያት (የጥናቱ አዘጋጅ የሆነው United Nations Development Programme - UNDP - እንደሚጠቁመው ) ሚዛናዊነቱን ያልጠበቀው ዓለማችንን በቴክኖሎገና በሣይንስ ውጤቶች ማንበሽበሽ በመሰኘት የሚታወቀው የዘመኑ የሥልጣኔአችን አርማ «Globalization» ነው። በጥናቱ መሠረት «unfettered globalization» በሚፈጥረው ወይም በፈጠረው ሚዛናዊ ዛቢያ ምክንያት የሚጠቀመው ጥቂቱ ወገን ብቻ ሲሆን፣ አብዛኛው ኅብረተሰብ ግን «የበይ ተመልካች» ሆኖ እየቀረ ነው። ይህ ክስተት በታዳጊ አገሮች ውስጥ ጐልቶ የሚታየው ከሠለጠኑት የአንደኛው ዓለም አገሮች በላይ ሲሆን፣ በአብዛኛው በታዳጊ አገሮች ውስጥ የሚገኘው የላይኛው የኅብረተሰብ ክፍል «first class, elites» ነጋዴውና ፖለቲከኛው በሥልጣን ላይ ያለው ... ) የዚህ የተዛባ የሃብት ስርጭት ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች ናቸው።

በመሠረቱ ዓለማችን አስጊ በሆነው የዘር መድሎ (apartheid) ጥቁር ጐዳና እያቀለቀለች የአዲሱን ሚሌኒያ ምዕተ-ዓመት ልትቀበለው መሆኑ የሚያስፈራ ነው። ይህ የዘር መድሎ የተመሠረተው በዘር ልዩነት ላይ ሣይሆን በብሔር ምንጭ ላይ ነው።

እኒያ የካፒታልና የንግድ ሥርጭት ያግዱ የነበሩ እንቅፋቶች እየፈረሱ ፣ እየጠፉ በሂዱ ቁጥር በምትካቸው አዲስ እየተተካ መሄዱ ... ።ያ የናጠጠ የዓለማችን ከበርቴ ብቻውን እነዚህን እንቅፋቶች እየዘለለና እየሠበረ በቢሊዮን የሚቆጠረውን ሕዝብ ጥሎት ይጋልባል።

ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ቢኖር ይህ በሃብታሙና በደሃው መሃከል ያለው የሃብት ስርጭት

ሚዛናዊነቱን ካለመጠበቁ የተነሣ የሚፈጥረው ልዩነት እየሠፋ፤ እያደገና እየተለጠጠ በሂደ ቁጥር፤

Ø የሰብአዊ መብቶች መረገጥ፤

Ø የፀጥታ መናጋት፤

Ø የአዳዲስ ጦርነቶች መቀስቀስ፤

በጥቅሉ የዓለማችን የፀጥታና ደህንነት መናጋት፤ ዓለማችን ከቀን ወደ ቀን ጥልቅ ወደሆነው ያፓርታይድ ገደል እየሰመጠች፤ የተባበሩት መንግሥታት ደግሞ ከዚሁ የባሱ አስደንጋጭ መረጃዎችን ማውጣቱ በመጪዎች ዓመታት ልናያቸው ወይም ልንጠብቃቸው የምንገደደቸው ክስተቶች ናቸው።

በዓለማችን ላይ ያለውን የኑሮ ልዩነት በመጠኑም ቢሆን ለመረዳት ከዚህ በታች ያለውን ዘንጠረዥ ይመልከቱ፤

| ተራ ቁ. | በጣም ደሃ ሐገሮች | የአንድ ዜጋ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በዶላር | በጣም ሃብታም ሐገሮች | የአንድ ዜጋዓመታዊ የነፍስወከፍ ገቢበዶላር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሱዳን | 36 | ሊይኽንሽታይን | 39 833 |
| 2 | ሳኦቶሜ | 49 | ሱዊዘርላንድ | 37 175 |
| 3 | ሞዛምቢክ | 77 | ጃፓን | 34 629 |
| 4 | ኤርትራ | 96ä | ሉክሰምበርግ | 29 857 |
| 5 | ኢትዮጵያ | 96ä | ኖርዌይ | 28 104 |
| 6 | ኮንጎ(ዛየር) | 117 | ዴንማርክ | 26 477 |
| 7 | ሶማሊያ | 119 | አሜሪካ | 26 037 |
| 8 | ታጃክስታን | 122 | ጀርመን | 25 860 |
| 9 | ካምቦዲያ | 130 | ኦስትሪያ | 25 578 |
| 10 | ጊኒ ቢሳው | 131 | ቤልጂግ | 25 949 |

ይህ የገቢ መጠን ኤርትራና ኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ከመግባታቸው በፊት የተሰላ በመሆኑ ባሁኑ ሰዓት የኤርትራናየኢትዮጵያ ዜጎች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢከዚህ በታች መውረዱ ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል።«ጦቢያ ጋዜጣ» ተመድን ገልፆ እንደገለፀው፤ 5ኛ ዓመት ቁጥር 4 የካቲት 4ቀን 1991 ዓ.ም